INTERME

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ማ/ቅ/ጽ/ቤት
EHTIOPIAN REVENUE AND CUSTOMS AUTHORITY

የውስጥመጻጻፊያ

ቁጥር፡ ም/ሥ/የአድ/07/334/07
ቀን ፡ 07/09/2007

- ለ፡ ጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም የሥራ ሂደት
- ለ፡ ገላን ተርሚናል ጉምሩክ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለ፡ ሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት
- ለ፡ መጋዘን አስተዳደርና ቁጥጥር የሥራ ሂደት
- ለ፡ ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የሥራ ሂደት
- ለ፡ ደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት
- ለ፡ በመንግስት የተሰጡ መብቶች ማስፈጸሚያ የሥራ ሂደት

- ከ፡ ጉምሩክ ጉዳዮች ም/ስራ አስኪያጅ
  <u>አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በቁጥር 3.3.0/737/07 በቀን 03 ግንቦት 2007 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሚያዚያ 20 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር ገ/ኢ/11/1/143 በተፃፈ ደብዳቤ የፓልም ዘይት በንግድ ሚኒስቴር በሚመረጡ ድርጅቶች አማካኝነት ከውጪ እየተገዛ በአገር ውስጥ እንዲሰራጭ መንግስት በወሰነው መሰረት ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ እንዲገባ፣ ከማናቸውም የአገልግሎት ክፍያ (Bank Charge,Scanning fee,Quaratine, Standard fee, or Inspection fee) ነፃ እንዲሆን እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ኢንሹራንስ አገልግሎት 50% ብቻ እንዲከፍል ገልፃችኋል፡፡ ስለሆነም ለተገቢው አፈፃፀምና ክትትል ይረዳ ዘንድ የተላከልንን 3 ገጽ ኮፒ ደብዳቤ በአባሪነት አያይዘን ልከንላችኋል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፣
- ለ፡ ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
- ለ፡ ሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ስራዎች ም/ሥራ አስኪያጅ
  <u>አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

Memo AZ - aw

0 3 ግንቦት 2007

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች
<u>በያሉበት</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሚያዝያ 20 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር ገ/አ/11/1/143 በተፃፈ ደብዳቤ የፓልም ምግብ ዘይት በንግድ ሚኒስቴር በሚመረጡ ድርጅቶች አማካኝነት ከውጭ እየተገዛ በአገር ውስጥ እንዲሠራጭ መንግስት በወሰነው መሠረት ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ እንዲገባ፣ ከማናቸውም የአገልግሎት ክፍያ (Bank Charge, Scanning fee, Quaratine, Standard fee, or Inspection fee) ነፃ እንዲሆኑ እና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ኢንሹራንስ አገልግሎት 50% ብቻ እንዲከፍል ያሳሰበበትን 2 ገጽ ደብዳቤ አባሪ እየላክን በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

አበበ አስፋው አድማሱ
የጉምሩክ ... ድጋፍና
ክትትል ዳይሬክቶሬት
ም/ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ፣</u>
- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራ ሂደት
<u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣</u>

.16

851
22/8/07

7/7/1521
22/8/07

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Development

ቁጥር 7/ኢ/11/1/143
Ref. No.

ቀን 20/08/2007
Date

ለንግድ ሚኒስቴር
ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
ለኢትዮጵያ መድን ድርጅት
ለኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና
ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን
ለኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የፓልም ምግብ ዘይት ወደአገር ውስጥ ሲገባ ስለሚጠየቀው ቀረጥ/ታክስና የአገልግሎት ክፍያን ይመለከታል፡-

መሠረታዊ ሸቀጦችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለሕብረተሰቡ ለማዳረስ ሲባል ስለሚጠየቀው ቀረጥ/ታክስ እና የአገልግሎት ክፍያን አስመልክቶ መስከረም 28 ቀን 2005 በቁጥር ገ/ኢ/ል/ሚ/11/1/102 ደብዳቤ የጻፍንላችሁ መሆኑ ይታወቃል፡፡

የፓልም ምግብ ዘይት ከመጋቢት 2003 ዓ.ም በሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጪ ድርጅት በኩል ከውጭ ተገዝቶ ወደ አገር ውስጥ እየገባ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም የፓልም ምግብ ዘይት የውጭም ሆነ የአገር ውስጥ ገበያ ዋጋ የተረጋጋ በመሆኑ በንግድ ሚኒስቴር በሚመረጡ ድርጅቶች አማካኝነት ከውጭ እየተገዛ በአገር ውስጥ እንዲሠራጭ መንግሥት ወስኗል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 3

.../2

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Development

ቁጥር ____________
Ref. No.

ቀን ____________
Date



ስለዚህ ከዚህ በፊት ይደረግ እንደነበረው ሁሉ የንግድ ሚኒስቴር የፓልም ምግብ ዘይትን ከውጭ በመግዛት በአገር ውስጥ እንዲያከፋፍሉ መርጦ በጽሑፍ ለሚገልጽላችሁ ድርጅቶች ከውጭ ገዝተው ወደአገር ውስጥ የሚያስገቡት የፓልም ምግብ ዘይት፣

ሀ) ከማንኛውም ቀረጥ/ታክስ ነጻ ሆኖ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ፣

ለ) ማንኛቸውም የአገልግሎት ጠያቂ ተቋሞች Bank Charge, Scanning fee, Quaratine, Standard fee, or Inspection fee ክፍያ እንዳያስከፍሉ

ሐ) የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እስከአሁን እየጠየቀ ካለው የInsurance አገልግሎት ክፊሉን ብቻ ማለት 50% ብቻ እንዲያስከፍል፣ መወሰኑን እያስታወቅን የንግድ ሚኒስቴርም የፓልም ምግብ ዘይት ከውጭ እንዲያስመጡ የመረጣቸውን ድርጅቶች ለሚመለከታቸው አካላት ከወዲሁ በጽሑፍ እንዲገልጽ እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፣
- ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
  አዲስ አበባ

ስልክ TEL 251-11-155 24 00, 22 66 98 251-11-155 00 81, 83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O. Box 1905, 1037
ፋክስ Fax. 251-11-155 13 55, 55 14 96 251-11-155 38 44
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ Addis Ababa-Ethiopia